በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የገንዘብ ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

MINISTER OF FINANCE

ቁጥር / Ref. No 7/ሺ1/2/131

ቀን / Date 04/02/2014

**ለገቢዎች ሚኒስቴር**
**<u>አዲስ አበባ</u>**

የሚኒስትሮች ም/ቤት የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንድ አንድ አንቀፆችን አፈፃፀም ግልፅ ለማድረግ እንዲሁም በአንድ አንድ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ጫናን ያሳደሩ የደንቡን አንቀፆች ለማሻሻል ለሚኒስትሮች ምክር ቤት በቀረበው የደንቡ ማሻሻያ ላይ ምክር ቤቱ መስከረም 13 ቀን 2014 ዓ.ም. ባካሄደው 100ኛ መደበኛ ስብሰባው በዝርዝር ተወያይቶ በማፅደቅ ደንቡ በሥራ ላይ እንዲውል ወስኗል።

ስለዚህ ለአፈፃፀም እንዲረዳችሁ በምክር ቤቱ ፀድቆ በሥራ ላይ እንዲውል ውሳኔ የተሰጠበትን የደንቡን ማሻሻያ ከነመግለጫው ከዚህ ጋር አባሪ አድርገን መላካችንን እንገልፃለን።

ከሠላምታ ጋር

እዮብ ተካልኝ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

ግልባጭ፣

ለሕግ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት
<u>ገንዘብ ሚኒስቴር</u>

ስልክ 251-11-155 24 00,22 66 98
የፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905,1037
ፋክስ/Fax 251-11-156 01 24 55 14 96
MoF_Ethiopia
facebook.com/MoFEDet

## የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብን ለማሻሻል ስለተዘጋጀው
## <u>ረቂቅ ደንብ የተዘጋጀ አጭር መግለጫ</u>

### 1. <u>መግቢያ</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 ከነሐሴ 3 ቀን 2009 ዓ.ም ጀምሮ በሥራ ላይ የዋለ ሲሆን፣ የኢትዮጵያ የገቢ ግብር ሥርዓት ዘመናዊ፣ ቀልጣፋና የአገሪቱን ኢኮኖሚ በተገቢው መንገድ መምራት የሚያስችል እንዲሆን በማድረግ ረገድ የበኩሉን አስተዋፅዖ በማበርከት ላይ ይገኛል።

ይሁን እንጂ አንድ አንድ የደንቡ አንቀፆች ግልፅነት የሚጎድላቸው እንዲሁም በአንድ አንድ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ጫናን ያሳደሩ ሆነው በመገኘታቸው እነዚህን የደንቡን አንቀፆች ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል።

### 2. <u>የማሻሻያው ዓላማ</u>

የማሻሻያው ዓላማዎች:-

2.1 ግልፅነት የጎደላቸው አንቀፆች በግብር ከፋዩና በግብር ሰብሳቢው መካከል በማስከተል ላይ ያሉትን ውዝግብ እና ይህም ውዝግብ ገቢው በወቅቱ እንዳይሰበሰብ በማድረግ ረገድ ያሳደረውን ተፅዕኖ መቅረፍ፣

2.2 በኢንቨስትመንት ላይ ጫናን ያሳደሩ አንቀፆችን በማሻሻል የኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣

ናቸው።

### 3. <u>የማሻሻያው ዋና ዋና ገፅታዎች</u>

#### 3.1 <u>የካፒታል ዕቃዎች የኪራይ ውል (አንቀጽ 34)</u>

በካፒታል ዕቃ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 እንደተደነገገው ሦስት ዓይነት የካፒታል ዕቃዎች የኪራይ ውል ያለ ሲሆን፣ እነዚህም የፋይናንስ ኪራይ፣ የአጭር ጊዜ የመጠቀሚያ ኪራይ እና የዱቤ ግዥ ናቸው።

በፋይናንስ ኪራይ እና በአጭር ጊዜ የመጠቀሚያ ኪራይ የንብረቱ ባለቤት አከራይ ሲሆን፣ በተዋዋይ ወገኖች ስምምነት መሰረት በውሉ ዘመን መጨረሻ የንብረቱ

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት

ባለቤትነት ወደተከራዩ ሊተላለፍ ይችላል፡፡ በዱቤ ግዥ ውል ግን ገዥው በከፈለው ገንዘብ መጠን የንብረቱ ባለቤት የሚሆን ሲሆን ዕዳውን ከፍሎ ሲያጠናቅቅ ያለምንም ቅድመ-ሁኔታ ሙሉ በሙሉ የንብረቱ ባለቤት ይሆናል፡፡

ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት በካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 አንቀጽ 16 የዱቤ ግዥ ስምምነትን በሚመለከት የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው ለተከራዩ መሆኑ በግልፅ ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ በገቢ ግብር ደንብ አንቀጽ 34(1) በሦስቱም ዓይነት የካፒታል ዕቃዎች ኪራይ ውል ተከራዩ የከፈለው የኪራይ ክፍያ ከጠቅላላ የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተቀናሽ የሚደረግና ለተከራዩ የእርጅና ቅናሽ የማይታሰብ መሆኑ ተመልክቷል፡፡

በዚህም ምክንያት የካፒታል ዕቃዎችን በዱቤ ግዥ ውል በመከራየት ሥራቸውን የሚያከናውኑ አነስተኛና ጥቃቅን ድርጅቶች ለንብረቱ ዋጋ ያወጡት ወጪ በአጭር ጊዜ ውስጥ በወጪ ተቀናሽ እንዲሆንላቸው የሚያስችለው የእርጅና ቅናሽ ተጠቃሚ ባለመሆናቸው ሥራ በጀመሩባቸው ዓመታት ከፍተኛ ግብር እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ፡፡

ይህንን ችግር ለማቃለል የገቢ ግብር ደንቡ ከካፒታል ዕቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ጋር በተጣጣመ መልኩ እንዲቀረፅ ተደርጓል፡፡

### 3.2. <u>በከፊል ለንግድ ሥራ በዋለ ህንፃ ላይ የሚታሰብ የእርጅና ቅናሽ (አንቀጽ 40)</u>

በህንፃ ሥራ አዋጅ የተደነገገውን በመከተል እንዲሁም ለታክስ አስተዳደር ያለውን አመቺነት ከግምት ውስጥ በማስገባት ለህንፃ የእርጅና ቅናሽ የሚፈቀደው የህንፃው ግንባታ ከተጠናቀቀ በኋላ እንደሚሆን ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ ከተጠናቀቀ በኋላ በከፊል ለንግድ ሥራ በከፊል ደግሞ ለሌላ አገልግሎት ስለሚውል ህንፃ የሚደነግገውን የደንቡን አንቀጽ 40 ሙሉ በሙሉ ሳይጠናቀቅ ለኪራይ የዋለ ህንፃ ላይ የእርጅና ቅናሽ እንዲሰላ የሚፈቅድ አንቀጽ እንደሆነ በመቁጠር ያለመግባባት ይፈጠራል፡፡

ይህንን ውዥንብር ለማጥራት አንቀጹ የሚመለከተው ሙሉ በሙሉ ግንባታው ከተጠናቀቀ በኋላ በከፊል ለንግድ ሥራ የዋለን ህንጻ መሆኑ በግልፅ እንዲመለከት ተደርጓል፡፡

የገንዘብ
የሪከርድ አስተዳደር አገልግሎት
2

## 3.3. ኪሣራን ስለማሸጋገር (አንቀጽ 42(1))

አንድ ግብር ከፋይ በንግድ ሥራ እንቅስቃሴ ውስጥ ባለበት ጊዜ ሊካካስለት የሚችለው ሁለት ጊዜ ያጋጠመ ኪሣራ እንደሆነ እና ይህም ኪሣራ የሚሸጋገረው ቢበዛ ለ5 ዓመታት ጊዜ እንደሆነ በገቢ ግብር አዋጁ ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ ግብር ከፋዩ ኪሣራውን ለማካካስ የሚችለው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ሲኖረው በመሆኑ በአምስቱ ዓመት ጊዜ ውስጥ ያጋጠመውን ኪሣራ ማካካስ የሚያስችል ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከሌለው ኪሣራው ከአምስት ዓመት በላይ ሊሸጋገር ይገባል የሚል ክርክር ይነሳል፡፡

በንግድ ሥራ ውስጥ ያለ ግብር ከፋይ ላልተወሰነ ጊዜ ኪሣራ እያጋጠመው በሥራው ሊቀጥል የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር ስለማይችል አዋጁ ሊካካስ የሚችለው ሁለት ጊዜ ያጋጠመ ኪሣራ ሆኖ በአምስት ዓመት ውስጥ መሆኑን በግልፅ የደነገገ ሆኖ ሳለ ለአንቀጹ የሚሰጠው ትርጉም የተሳሳተ ነው፡፡

ይህንን ግልጽ ለማድረግ በአምስቱ ዓመት ውስጥ ግብር ከፋዩ ቀድሞ ካጋጠመው የሁለት ጊዜ ኪሣራ በላይ ተጨማሪ ኪሣራ አጋጥሞኛል የሚል የገቢ ማስታወቂያ የሚያቀርብ ከሆነ ኪሣራው ከተጠቀሰው ጊዜ በኋላ ሊሸጋገር የማይችል መሆኑ ግልፅ ተደርጓል፡፡

## 3.4 የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ

በገቢ ግብር ደንቡ አፈፃፀም ረገድ አስቸጋሪ ከነበሩት ድንጋጌዎች አንዱ የውጭ አገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራን የሚመለከተው ድንጋጌ ነው፡፡

ከባንኮች ውጪ ያሉ ሌሎች የንግድ ሥራ ድርጅቶች ለካፒታል ንብረት ማፍሪያ የወሰዱትን ብድር በሚከፍሉበት ወይም በውጭ ምንዛሪ ሌሎች የንግድ ሥራ እንቅስቃሴዎችን በሚያከናውኑበት ጊዜ የውጭ ምንዛሪ ኪሣራ ያጋጥማቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ የገቢ ግብር ደንቡ በውጭ ምንዛሪ ግብይት የደረሰ ኪሣራ ሊካካስ የሚችለው በውጭ ምንዛሪ ግብይት ከተገኘ ጥቅም ጋር ብቻ እንደሆነ ስለሚደነግግ እና እነዚህ ድርጅቶች የውጭ ምንዛሪ የማይዙ በመሆኑ ከግብይቱ የሚያገኙት ጥቅም ስለሌለ ለከፍተኛ ችግር ሲዳረጉ ቆይተዋል፡፡

ይህንን ችግር ለማቃለል በውጭ ምንዛሪ ግብይት ያጋጠመ ኪሣራ ለሁለት ተከፍሎ፣

የገንዘብ
የሕግ ማስተዳደር
አገልግሎት

- የውጭ ምንዛሪ ግብይቱ የተፈፀመው ከካፒታል ንብረት ግዥ ጋር በተያያዘ ከሆነ ኪሣራው የካፒታል ንብረቱ የተገዛበት ዋጋ ላይ ተደምሮ ለእርጅና ቅናሽ መሠረት እንዲሆን፣
- የውጭ ምንዛሪ ግብይቱ የተፈፀመው ከካፒታል ንብረቱ ግዥ ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ ከሆነ ኪሣራው በግብር ዘመኑ እንደወጪ እንዲያዝ፣

በሚያስችል አኳኋን አንቀጹ ተሻሽሏል፡፡

3.5 <u>የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር (አንቀጽ 56(1))</u>

የካፒታል ዋጋ ዕድገት ጥቅም ግብር የሚከፈለው ለንግድ ሥራ የተያዘን ህንፃ ወይም አክሲዮንን በማስተላለፍ በሚገኝ የዋጋ ዕድገት ጥቅም ላይ ነው፡፡

ይሁን እንጂ የገንዘብን የመግዛት አቅም መቀነስ ተከትሎ የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ እንዲደረግ የገቢ ግብር ደንቡ የሚፈቅደው ለህንፃ ብቻ በመሆኑ፣ አክሲዮን የሚሸጡ ግብር ከፋዮች የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ሳይደረግ የአክሲዮን ሰነዱ ላይ በተፃፈው ዋጋ (Par Value) እና በተሸጠበት ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት ጥቅም እንደሆነ ተቆጥሮ ግብር እንዲከፍሉ ይጠየቃሉ፡፡

ይሁን እንጂ በገቢ ግብር አዋጁ እንደተመለከተው ግብር ከፋዩ በትክክል አግኝቷል ሊባል የሚችለው ጥቅም በአክሲዮኑ የወቅቱ ዋጋ እና በተሸጠበት ገንዘብ መካከል ያለው ልዩነት ስለሆነ ከአክሲዮን ሽያጭ ለሚገኝ የዋጋ ዕድገት ጥቅምም የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ እንዲፈቀድ በሚያስችል አኳኋን አንቀጹ ተሻሽሏል፡፡

3.6 <u>ተካክሶ ያልተጠናቀቀ ኪሣራ (አንቀጽ 68)</u>

ግብር ከፋዮች ቀደም ሲል በሥራ ላይ በነበረው አዋጅ ሁለት ኪሣራ የተካካሰላቸው ቢሆንም በአዲሱ አዋጅ መሰረት ተጨማሪ ሁለት ኪሣራ ሊካካስላቸው እንደሚገባ ይጠይቃሉ፡፡

በመሆኑም ለዚህ ጥያቄ መሰረት የሆነው ግልፅነት የጎደለው አንቀጽ እንዲሻር እና ሊካካስ የሚችለው ከሁለት ዓመት ኪሣራ ውስጥ ያልተካካሰው ቀሪ መጠን ብቻ መሆኑ ግልፅ እንዲሆን ተደርጓል፡፡

4. <u>የደንቡ ተፈፃሚነት</u>

ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት የደንቡ ድንጋጌዎች ጋር በተያያዘ በተፈጠረ ያለመግባባት በርካታ ጉዳዮች ውሳኔ ሳያገኙ በእንጥልጥል ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም ችግሩን ወጥ በሆነ መልኩ ለመፍታት ክፍያ ያልተፈፀመባቸው ከተዘረዘሩት ጉዳዮች ጋር የተያያዙ የግብር ጉዳዮች በዚህ ደንብ መሠረት ፍፃሜ የሚያገኙ መሆኑን የሚገልፅ ድንጋጌ እንዲካተት ተደርጓል፡፡

ስለዚህ የገቢ ግብር ደንቡ ማሻሻያ በሥራ ላይ እንዲውል እንዲፈቀድ ይህ አጭር መግለጫ ቀርቧል፡፡

የገንዘብ
የፌዴራል
ሰብትዳደር
አገልግሎት

# የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ___/2014

## የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብን ለማሻሻል የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 አንድ አንድ አንቀፆች የአፈፃፀም ግልፅነት የሚጎድላቸው በመሆኑ፤

በአንድ አንድ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ላይ ጫናን ያሳደሩ የደንቡን አንቀፆች ማሻሻል በማስፈለጉ፤

ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ደንቡን ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የሚኒስትሮች ምክር ቤት በፌዴራል የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 አንቀጽ 99 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ (ማሻሻያ) ቁጥር ____/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ማሻሻያ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የፌዴራል የገቢ ግብር ደንብ ቁጥር 410/2009 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1/ የደንቡ አንቀጽ 34 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 34 ተተክቷል፡-

"34. **በካፒታል ዕቃዎች የኪራይ ውል መሠረት ለተያዘ የንግድ ሥራ ሀብት የሚፈቀድ ተቀናሽ**

1) በፋይናንስ ኪራይ ወይም በአጭር ጊዜ የመጠቀሚያ ኪራይ ውል መሠረት ለተያዘ የንግድ ሥራ ሀብት የሚፈፀም የኪራይ ክፍያ ከጠቅላላ የንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፤

2) በዱቤ ግዥ ውል መሠረት በተያዘ የንግድ ሥራ ሀብት ላይ የእርጅና ቅናሽ የሚሰላው ለዱቤ ገዥው ነው፤

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ተቀናሽ የተፈቀደለት ሰው በንብረቱ ላይ የእርጅና ቅናሽ አይታሰብለትም፤

4) ለዚህ አንቀፅ ዓላማ የፋይናንስ ኪራይ፣ የአጭር ጊዜ የመጠቀሚያ ኪራይ እና የዱቤ ግዥ ውል የሚሉት ሀረጎች በካፒታል እቃ ኪራይ ንግድ ሥራ አዋጅ ቁጥር 103/1990 የተሰጣቸውን ትርጉም ይይዛሉ።"

2/ የደንቡ አንቀጽ 40 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 40 ተተክቷል።

" 40 <u>በከፊል ለንግድ ሥራ በዋለ ሕንፃ ላይ የሚታሰብ የእርጅና ቅናሽ</u>

አንድ ሕንፃ ሙሉ በሙሉ ከተጠናቀቀ በኋላ በከፊል በንግድ ሥራ ሀብትነት በሚያገለግልበት ጊዜ የእርጅና ቅናሽ የሚታሰበው ለንግድ ሥራ አገልግሎት በዋለው መጠን ብቻ ይሆናል።"

3/ የደንቡ አንቀጽ 42(1) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 42(1) ተተክቷል።

"1. አንድ ግብር ከፋይ በገቢ ግብር አዋጁ አንቀጽ 26 - 38 ወይም 46 መሠረት ከአንድ የግብር ዓመት በላይ የሚሸጋገር ኪሣራ ያጋጠመው እንደሆነ በመጀመሪያ ያጋጠመው ኪሣራ በቅድሚያ ይካካስለታል፤ ሆኖም ኪሣራው የሚካካሰው ግብር የሚከፈልበት ገቢ ያለው በሚሆንበት ጊዜ ሲሆን፣ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ከሌለው ኪሣራው በአዋጁ ከተደነገገው ጊዜ በላይ ሊሸጋገር አይችልም።"

4/ ከደንቡ አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 4 ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 5 ተጨምሯል፤

"42(5) ሚኒስትሩ በቂ ምክንያት መኖሩን ሲያምንበት በማምረት ዘርፍ የተሰማራ ግብር ከፋይ ለሶስተኛ ጊዜ የሚያጋጥመው ኪሳራ እንዲሸጋገር ሊፈቅድ ይችላል።"

5/ የደንቡ አንቀጽ 44(2) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 44(2) ተተክቷል።

"44(2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣

ሀ) ግብር ከፋዩ በአንድ የግብር ዓመት ውስጥ የውጭ ሀገር ገንዘብ ምንዛሪ ኪሣራ ያጋጠመው እንደሆነ እና፡-

(i) ኪሣራው ከካፒታል ንብረት ግዥ ጋር የተያያዘ ከሆነ የኪሣራው መጠን ለእርጅና ቅናሽ መሠረት በሆነው የንብረት ዋጋ ውስጥ ይካተታል፣

(ii) ኪሣራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ(i) ከተመለከተው ውጪ ከሥራ እንቅስቃሴ ጋር የተያያዘ ከሆነ ኪሣራው በደረሰበት የግብር ዘመን በወጪነት ይያዛል፣

ለ) ግብር ከፋዩ የደረሰበትን ኪሣራ መጠን ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ የሚዘረዝሩ ማስረጃዎችን በማቅረብ ማረጋገጥ አለበት።"

6/ የደንቡ አንቀጽ 56 (1) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 56(1) ተተክቷል

"56(1) በአዋጁ የተመለከተው የምድብ "ሀ" እና "ለ" ግብር የሚከፈልበት ሀብት ዋጋ ሚኒስትሩ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የዋጋ ግሽበት ማስተካከያ ይደረግበታል።"

7/ የደንቡ አንቀጽ 68 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 68 ተተክቷል።

"68. <u>የንግድ ሥራ ኪሣራን ስለማሸጋገር</u>

በተሻረው አዋጅ መሠረት ተቀናንሶ ያላለቀ የንግድ ሥራ ኪሣራ ያለው ግብር ከፋይ ኪሣራው በተሻረው አዋጅ መሠረት ሙሉ በሙሉ ያልተቀናነሰ ከሆነ ቀሪው ኪሣራ በተሻረው አዋጅ መሠረት ይቀነስለታል።"

3. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

1/ ይህ ደንብ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ ደንብ ከተደነገጉት ጋር በተያያዘ ክፍያ ያልተፈፀመባቸው የግብር ጉዳዮች በዚህ ደንብ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ።

አዲስ አበባ ________ ቀን 2014 ዓ.ም

አብይ አህመድ (ዶ/ር)
የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ጠቅላይ ሚኒስትር

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION NO.___/2021**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATIONS TO AMEND THE INCOME TAX REGULATIONS**

WHEREAS, certain provisions of the Council of Ministers Federal Income Tax Regulations No. 410/2016 lack sufficient clarity for application;

WHEREAS, it is necessary to amend certain provisions of the Regulation that are found to entail negative impact on some economic activities;

WHEREAS, for the above-mentioned reasons, it has become necessary to amend the Regulation;

NOW THEREFORE, the Council of Ministers issued this Regulation pursuant to the power vested in it under Article 99 of the Federal Income Tax Proclamation No. 979/2016.

1. **SHORT TITLE**

This Regulation may be cited as "Council of Ministers Federal Income Tax Regulation (Amendment) No. ___2021".

2. **AMENDMENT**

Council of Ministers Federal Income Tax Regulations No. 410/2016 is amended as follows:

1. Article 34 of the Regulations is deleted and replaced by the following new Article 34.

"34. **Deduction allowed for Business Asset held under Capital Lease Agreement**

1. Lease payment made for business asset held under Financial Lease or Operating Lease Agreement is deductible business expenditure from gross business income.

2. In the case of a Hire Purchase Agreement, the Lessee shall have depreciation allowance on the asset.

3. A person realizing deduction under sub-article (1) of this Article shall not be entitled to depreciation on the asset.

4. For the purpose of this Article, the terms Financial Lease, Operating Lease and Hire Purchase shall have the meanings ascribed to them under the Capital Goods Leasing Business Proclamation No. 103/1998."

2. Article 40 of the Regulations is deleted and replaced by the following new Article.

"40. **Depreciation Allowed on a Building used Partially as a Business Asset**

Depreciation on a fully completed building used partially as a business asset shall be allowed only in proportion to the portion of the building used as a business asset. "

3. Article 42(1) of the Regulations is deleted and replaced by the following new Article 42(1):

"42 (1) If a taxpayer has a loss carried forward under Articles 26, 38 and 46 of the Income Tax Proclamation for more than one tax year, the loss of the earlier year shall be deducted first. However, the loss shall only be deducted if the taxpayer has a taxable income and the loss shall not in any circumstance be forwarded beyond the period prescribed by the Proclamation."

4. The following new sub -article 5 is added after sub-article 4 of Article 42;

"5. The Minister may for good cause allow a third loss suffered by a taxpayer engaged in the manufacturing sector to be carried forward. "

5. Article 44(2) of the Regulation shall be deleted and replaced by the following new Article 44(2):

" 44(2) Subject to the provisions of sub-article 3 of this Article:

a ) If a taxpayer incurs a foreign currency exchange loss during a tax year; and

i) if the loss is related with the purchase of capital goods, the expenditure shall be made part of the value of the capital good used as a basis for depreciation;

ii) if the loss is incurred for operating expenses other than those under sub-article 1 of this Article, such loss shall be made part of the expenses of the fiscal year.

b) The tax payer has the obligation to prove the loss by submitting evidences to be prescribed in a directive issued by the Tax Authority."

6. Article 56(1) of the Regulation is deleted and replaced by the following new Article 56(1):

"56(1) The cost of Class "A" and Class "B" taxable asset provided in the Proclamation shall be adjusted for inflation as determined under a directive issued by the Minister."

7. Article 68 of the Regulation is deleted and replaced by the following new Article 68:

"68. **Business Loss Carried Forward**

A taxpayer who has a business loss under the repealed Proclamation that has not been fully deducted under the repealed Proclamation shall continue to be deducted in accordance with the repealed Proclamation. "

## 3. EFFECTIVE DATE

1. This Regulation shall enter into force on the date of its publication in the Federal Negarit Gazette.

2. Notwithstanding the provisions of sub-article 1 of this Article tax arrears resulting from tax matters provided under this Regulation shall be settled in accordance with this Regulation.

**Addis Ababa____day of______2021**

**Abiy Ahmed (PhD)**
**Prime Minister of the Federal Democratic Republic of Ethiopia**

